Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF REVENUE

ቁጥር 06/ጉ4/37/4
Ref. No
ቀን 03 መጋቢ 1996
Date

ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዕርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ይመለከታል፤

ቀደም ሲል በቁጥር 01/ጉ2/44/12 የካቲት 18 ቀን 1995 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ሸኚነት በዲፕሎማቶች አማካይነት ከጉምሩክ ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡ ዕቃዎች ብቻ በመቅረጫ ዋጋቸው ላይ የሚታሰብ የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ መመሪያ መተላለፉና እስካሁን ድረስ ሲሠራበት መቆየቱ ይታወሳል::

ሆኖም የዚህ ዓይነቱን የዕርጅና ስሌት አሠራር በአጠቃላይ ግልፅ እና አንድወጥ ሆኖ እንዲፈፀም ማድረጉ ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ወደ ሌላ ወገን ሲተላለፉ በተጠቃሚው ላይ እና በአስፈፃሚው በጉምሩክ ባለሥልጣን የሥራ አፈፃፀም ላይ ሲያስከትል የቆየውን ችግር እንደሚያቃልል እና ለተጀመረውም የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮግራም አጋዥ እንደሚሆን ስለታመነበት ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል::

በዚህም መሠረት ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው መመሪያ 6 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሆኖ የተላከ ስለሆነ ተግባራዊ እንዲደረግና ተጠቃሚዎችም እንዲያውቁት አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ እንዲገለፅ አሳስባለሁ::

ከሰላምታ ጋር

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

ግልባጭ

- ለም/ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለገቢዎች ኦፕሬሽንና ኢንተሊጀንስ መምሪያ
- ለቀረጥ ነፃ ማስፈፀሚያ መምሪያ
- ለሕግ አገልግሎት
- ለሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት
  ገቢዎች ሚኒስቴር
- በዝርዝር ለተመለከቱት
  በያሉበት

ስልክ Tel. 66 74 66 ፖ.ሣ.ቁ. P.O.BOX 2559 ፋክስ Fax 662628: 668244: 668246 E-mail:MOR@telecom.net.et አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
- ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን
- ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን
- ለፌዴራል የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን
- ለትግራይ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለአፋር ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለአማራ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለኦሮሞ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ መስተዳድር
- ለሱማሌ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለሐረሪ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለጋምቤላ ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለቤኒሻንጉል ብ/ክ/ መስተዳድር
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
- ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

<u>በያሉበት</u>

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

# የገቢዎች ሚኒስቴር
## መመሪያ ቁጥር 3/1996

## ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዕርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደሀገር የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት የዕርጅና ዘመን ቅናሽን በተመለከተ የመብቱ ተጠቃሚ በሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ለመፈፀም እንዲቻል ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል::

1. አውጭው ባለሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 84/2 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::::

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዕርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 3/1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

3. ትርጓሜ

1. «የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ» ማለት በሕግ ወይም በመመሪያ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ለማስገባት የተፈቀደለት ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ማናቸውም ሰው ነው::
2. «ዕቃ» ማለት ማንኛውም የመጓጓዣ ተሽከርካሪ፣ መሣሪያ ፣ የቢሮ መገልገያና የግል መገልገያ ዕቃ ነው::
3. «መንግሥት መ/ቤት» ማለት ማናቸውም በበጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው::
4. «ተሽከርካሪ» ማለት በሞተር ኃይል በመንገድ የሚንቀሳቀስ የሰውና የጭነት መጓጓዣ ከነመለዋወጫው ሲሆን ብስክሌትንም ይጨምራል::
5. «መሣሪያ» ማለት ማንኛውም የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ የካፒታል ዕቃ ነው::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

6. «የመቅረጫ ዋጋ» ማለት ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ጊዜ የነበረው የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ነው።

7. «የግል መገልገያ» ማለት ለግል የቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል ዕቃ ሲሆን ተሽከርካሪዎችንና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችን አይጨምርም።

8. የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 (እንደተሻሻለ) የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

4. *የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን*

1. የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ለመንግሥት መ/ቤት አገልግሎት ወደሀገር ውስጥ በመጡና በጊዜያዊነት ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

2. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከቀረጥ ነፃ ተደርገው በአገልግሎት ላይ ያሉና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የቀረጥ ነፃ መብት ላላቸው ባለመብቶች በተላለፉ ዕቃዎች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

5. *ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን ስለማስተላለፍ*

1. የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 54 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ በተመለከተው የዕርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ማስተላለፍ ይቻላል።

2. የዕቃው የእርጅና ቅናሽ ስሌት የሚታሰበው በዕቃው የመቅረጫ ዋጋ ላይ ሆኖ ዕቃው ወደአገር ውስጥ ከገባበት ቀን አንስቶ ይሆናል።

6. *የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ስለሚከፈልበት ሁኔታ*

1. ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ ያስገባው ወይም ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የተደረገው ዕቃ የእርጅና ዘመን ከማለቁ በፊት የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሲያስተላልፍ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስትና አራት መሠረት የእርጅና

Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ቅናሽ ምጣኔው በመቅረጫ ዋጋ እና ፀንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሠረት ቀረጡ ታስቦ ይከፈላል:: ሆኖም የመቅረጫ ዋጋቸው ብር 3,000.00 (ሦስት ሺህ) እና ከዚያ በታች የሆኑ የግል መገልገያ ዕቃዎች ለሌላ ሦስተኛ ወገን ሲተላለፉ ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም::

2. የዕቃው አገልግሎት በሙሉ ዓመት በማይገለፅበት ጊዜ ዕቃው የገባበትን ቀን መሠረት በማድረግ መንፈቅ እና ከዚያ በላይ ያገለገለ ከሆነ ብቻ ወደ ቀጣዩ ዓመት በማስጠጋት የአገልግሎት ዕድሜው እንዲታሰብ ይደረጋል::

3. ከቀረጥ ነፃ የገባው ዕቃ የዕርጅና ዘመኑ ከማለቁ በፊት እንደ እሳት ቃጠሎ፣ የግጭት አደጋ በመሳሰሉት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፣ ባለበት ሁኔታ ለማስተላለፍ አግባብ ባለው ባለሙያ ወይም ተቋም ተገምቶ የተገኘው ዋጋ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል::

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚው ከቀረጥ ነፃ የገባው ዕቃ የዕርጅና ዘመን ከማለቁ በፊት ለመንግሥታዊ መ/ቤት በስጦታ የሚያስተላልፈው ከሆነ ቀረጥ እንዲከፍል አይጠየቅም:: ሆኖም የጉምሩክ ባለሥልጣን ስጦታው የተላለፈለትን መ/ቤት ማንነት፣ የዕቃውን ዓይነት ዝርዝርና ዋጋ እንዲሁም ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ልክ መዝግቦ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳውቃል::

## ሠንጠረዥ አንድ

## የግል መገልገያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| ወደ ሀገር ከገባ በኋላ የአገልግሎት ዘመን | የአገልግሎት ዘመን ቅናሽ መቶኛ በአንዱ ዕቃ መቅረጫ ዋጋ ላይ | |
|---|---|---|
| | መቅረጫው ዋጋ ከ3,000 ብር በላይና ከ10,000ብር በታች ከሆነ | መቅረጫ ዋጋው ብር 10,000 እና ከዚያ በላይ የሆነ እንደሆነ |
| 1 ዓመት | 25 ከመቶ | 20 ከመቶ |
| 2 « | 50 « | 40 « |
| 3 « | 75 « | 60 « |
| 4 « | 100 « | 80 « |
| 5 « | - | 100 « |

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## ሠንጠረዥ ሁለት

## የተሽከርካሪዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን አገር ውስጥ ከገባ በኋላ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ |
|---|---|
| 1 ዓመት | 10 |
| 2 « | 20 |
| 3 « | 30 |
| 4 « | 40 |
| 5 « | 50 |
| 6 « | 60 |
| 7 « | 70 |
| 8 « | 80 |
| 9 « | 90 |
| 10 « | 100 |

## ሠንጠረዥ ሦስት

## የቢሮ መገልገያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን በአገር ውስጥ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ |
|---|---|
| 1 ዓመት | 20 |
| 2 « | 40 |
| 3 « | 60 |
| 4 « | 80 |
| 5 « | 100 |

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## ሠንጠረዥ አራት

## የመሣሪያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን አገር ውስጥ ከገባ በኋላ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ ላይ |
|---|---|
| 1 | 0 |
| 2 | 5 |
| 3 | 10 |
| 4 | 20 |
| 5 | 30 |
| 6 | 40 |
| 7 | 50 |
| 8 | 60 |
| 9 | 70 |
| 10 | 80 |
| 11 | 90 |
| 12 | 100 |

7. መረጃ ስለመያዝ እና በተጠየቀም ጊዜ ስለመስጠት

1. የጉምሩክ ባለሥልጣን ከቀረጥ ነፃ የሚገባ ማንኛውንም ዕቃ የመቅረጫ ዋጋው ሦስት ሺ(3,000.00) ብር እና ከዚያ በታች ከሆነው በስተቀር በጽሑፍ መዝገብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ(በኮምፒዩተር) መዝግቦ ይይዛል:: የመረጃው መዝገብ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል::

ሀ. የአስመጪው ወይም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚው ሙሉ ስምና አድራሻ
ለ. የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ቁጥርና ቀን
ሐ. የዕቃው ዓይነት ሞዴል፣ የተሠራበት አገር
መ. የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ በአሜሪካን ዶላር

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

2. የጉምሩክ ባለሥልጣን ከቀረጥ ነፃ ስለገቡት ዕቃዎች አግባብ ባለው ሰው ወይም አካል መዝግቦ ስለያዛቸው ዕቃዎች መረጃ እንዲሰጥ በተጠየቀ ጊዜ የመስጠት ኃላፊነት አለበት::

## 8. *የተሻሩ መመሪያዎች*

1. ከዚህ ቀደም ከቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ሲተላለፍ የዕርጅና ቅናሽን በማስላት ቀረጥና ታክስ ስለሚከፈልበት ሁኔታ የወጡ ማንኛውም መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረው፣ ተተክተዋል::
2. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ድንጋጌ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተፈፃሚነት አይኖረውም::

## 9. *መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል::

አዲስ አበባ